

እውነትን በፍቅር እንነጋገር
የነፍሴ ጥያቄዎች
ሒሩ ዋኘ

**ለወዳጄ ..........................................**

# መግቢያ

በሆነ ምክንያት ነፍሳችሁ በጥያቄ አጣድፋችሁ ታውቃለች? እኔ ግን ብዙ ጊዜ አጋጥሞኛል፡፡ አንዴ የእስልምና ዳኢዎች ስለ ክርስትናና ስለ እስልምና፣ ስለ ገነትና ስለ ገሃነመ እሳት ሲያወሩ የሰማሁበትን ቀን ግን ፈጽሞ አልረሳውም፡፡ ይህ አጋጣሚ እውነቱን ካልመረመሩ በስተቀር መልካም አይሆንም ብዬ እንዳስብ ስላደረገኝ ቁርአንንና የነቢዩ ሙሃመድን ሃዲሳት እንዲሁም የሲራ መጻህፍቱን ማገላበጥ ጀመርኩ፡፡ እነዚህን መጽሃፍት ባነበብኳቸው ቁጥር ግን በቁርአንና በነቢዩ ሙሃመድ የአላህ መልዕክተኝነት ዙሪያ በርካታ ጥያቄዎች በነፍሴ ውስጥ ምላሽ ፍለጋ ያጣድፉኝ ጀመር፡፡ ለአምላክ ምስጋና ይድረሰውና እኔ ብዙም ሳልቆይ ለጥያቄዎቼ ምላሽ ያገኘሁላቸው ቢሆንም መጀመሪያ በገጠመኝ ነገር እናንተም እንደኔው አጋጥሟችሁ ይሆናል ወይንም ወደ ፊት ሊያጋጥማችሁ ስለሚችል፣ ሙስሊም ከሆኑ ደግሞ እየተጓዙበት ያለውን የዘለአለም መንገድ ትክክለኛነት ለመመርመርና ለመገምገም እንዲያስችልዎት በማሰብ እራሴው ከነፍሴ የተጠየኳቸውን ጥያቄዎች እናንተን ልጠይቃችሁ ፈልጌአለሁ፡፡ ጥያቄዎቼን ከማቅረቤ በፊት ቅድሚያ ለጥያቄዎቼ መግቢያ ወይንም መነሻ የሚሆኑኝን እናንተንም ወደ መደምደሚያ ነጥብ ላይ እንድትደርሱ የሚያስችሏችሁን አንዳንድ አሳቦችን ከቁርአንና ከሃዲሳቱ መጻህፍት የወሰድኳቸውን ላስነብባችሁ ያስፈልገኛል፡፡

# የነፍሴ ጥያቄዎች

ከሞት በኋላ ሕይወት እንዳለና ሰዎች የአላህን መንገድ በመከተላቸው ለዘላለም በደስታ፣ ወይም ባለመከተላቸው በብዙ መከራ፣ ለዘለአለም የሚኖሩባቸው ገነትና ገሃነመ እሳት የሚባሉ ስፍራዎች መኖራቸውን የሚያምን ሃይማኖት ስለነሱ ሲያወራ ስለ አላህ፣ የሰው ልጆች ሁሉ ጠላት ስለ ሆነው ሰይጣን፣ በሰዎችና በአላህ መካከል ስለሚገኙ ነቢያት ማውራቱ የማይቀር ነው፡፡ ለአንድ ሰው ገነት ወይም ገሃነም መግባት አላህ፣ ሰይጣን፣ ነቢያቱና የአላህ ቃል ዋጋቸው ትልቅ ነው፡፡ ከላይ የጠቀስኳቸው ዳኢዎች በወቅቱ ሲናገሩ የሰማሁትና እኔም የተጋራሁት አሳብ፣ ጀነት ለመግባት በአላህና በነቢያቱ በማመን ለቃሉ መገዛትን ሲጠይቅ ገሃነም ደግሞ አላህንና ቃሉን ወደ ጎን በመተው ሰይጣንንና ሐሰተኛ ነቢያትን በመከተል የሚገቡበት የዘላለም ቤት ነው ያሉትን ነው፡፡ አላህ ሰዎች ለዘለአለም ከሰይጣን ጋር በገሃነም እሳት እንዳይሰቃዩ የሚመሩበትን ቃል አስይዞ እውነተኛ ነቢያትን ሲልክ ሰይጣንም ከእርሱ ጋር ለዘለለም በገሃነመ እሳት እንዲቀጡ እውነተኛ ነቢያት በማስመሰል ሃሰተኛ ነቢያቱን ልኳል፡፡ መጽሃፍ ቅዱስ ሲናገር

2 ቆሮ 11 ፡ 14-15

> <u>ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና</u>፡፡ እንግዲህ <u>አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ</u> ታላቅ ነገር አይደለም <u>ፍጻሜአቸውም እንደ ስራቸው ይሆናልና</u>

ስለዚህ አምላካቸውን የሚወዱና ዘላለማዊ ደስታን የሚናፍቁ ሁሉ በሐሰተኞችና በሰይጣን ላለመታለል እውነተኛው ነቢይና ትክክለኛው የአላህ ቃል የትኛው ነው? ወደ እስልምና ስንመለስ ደግሞ እውን ዳኢዎቹ እንደሚሉት ቁርአንና ነቢዩ ሙሐመድ የአላህ መልዕክትና መልዕክተኛ ናቸውን? የሚል ጥያቄ ማንሳትና ትክክለኛ ምላሽ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ የሰው ልጆች ግልጽ ጠላት የሆነው ሰይጣን ባለበት ሐሰት አለ፣ ለእርሱና ለተከታዮቹ ገሃነምና የዘለአለም መከራ ከአላህ ዘንድ ተቀጥሯል፡፡ ስለዚህ ከዚህ የሰው ልጆች ሁሉ ጠላት ከሆነው ጋር ለዘለአለም በገሃነም ላለመኖር ሰው አመንኩ ብሎ የሚከተለው ሃይማኖት እውነተኛ የአላህ መንገድ መሆኑን በጥንቃቄ ሊመረምርና ሊያረጋግጥ ይገባዋል እላለሁ፡፡ የአንድ ነቢይ እውነተኛነት ከሚለካባቸው መንገዶች መካከል ስለ አላህና ስለ ሰይጣን፣ እንዲሁም የራሱ የነቢዩ ሕይወትና አገልግሎት ከቀደሙት እውነተኛ ነቢያት ሕይወትና አገልግሎት ጋር ሲነጻጸር የሚገኘው ምስል አንዱ ነው፡፡ ለዚህ ነው ነቢዩ

ሙሐመድና ቁርአን ይህንን መለኪያ ያልፉት ይሆን? የሚል የነፍሴን ጥያቄ ጅማሬ ይዤ ወደ መጽሐፍቱ የሄድኩት፤ ሁሉም እዛው ይገኛል፡፡

የነቢዩ ሙሐመድን እውነተኛ ነቢይነት ለማረጋገጥ ምርመራዬን የጀመርኩት ቁርአንና የነቢዩ ሙሐመድ ሐዲሳት ስለ ሰይጣን ከዘገቡት ነበር፡፡ እነዚህ መዛግብት የሰው ልጆች ገነት በመግባት ዘላለም በደስታ እንዳይኖሩ በተለያየ መንገድ እንቅፋት ስለሚያስቀምጠው ስለ ሰይጣን ማንነት፣ ከሰው ልጆችና ከአላህ ጋር ስላለው ህብረት፣ ስለተፈጠረበት አላማና ተግባሩ፣ የሰው ልጆች በፍጻሜው ወደ ገነትና ወደ ገሃነመ እሳት ለመግባታቸው ስላለው ድርሻ፣ እንዲሁም ከነቢዩና ከመላው ሙስሊም ወገኖቻችን ጋር ስላላቸው ህብረት በርካታ ነገሮችን ዘግበው እናገኛለን፤ ከነዛ መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

# ሰይጣን ማን ነው?

ቁርአንና የነቢዩ ሙሐመድ ሃዲሳት ሰይጣን ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ መልሳቸውን እንዲህ አስፍረዋል፡-

1. አዳም ከመፈጠሩ በፊት እርሱና ዘሮቹ በጅነት ከመልአክት ጋር አብረው በአንድነት እየኖሩ በዛም መልኩ ልክ እንደ መላእክት መልክ ይመስል ነበር፡፡ አላህ አዳምን ከፈጠረው በኋላ ከመላዕክት ጋር ለአዳም እንዲሰግድ በታዘዘ ጊዜ ፈቃደኛ ባለመሆኑ አላህ ምህረት በሌለው በማይሻር ዘለአለማዊ እርግማን እረግሞታል፡፡ እርግማኑን በሰይጣንና በዘሮቹ ላይ ባስተላለፈበት ወቅት ወዲያው መልኩና ድምጹ ወደ ሌላ አይነት ድምጽ እንደተቀየረ የነቢዩ ሐዲሳት ዘግበዋል፤ ሙፈሲሮችም ይህንኑ በቁርአን ማብራሪያቸው ላይ አስተላልፈዋል:

**ሱረቱል አል-ሒጅር 15 ፡ 26-34**

ሰውንም ከሚቅጨለጨል ሸክላ ከሚገማም ጥቁር ጭቃ በእርግጥ ፈጠርነው፡፡ ጃንንም (ከሰው) በፊት ከእሳት ነበልባል ፈጠርነው፡፡ ጌታህም ለመላእክት ባለ ጊዜ (አስታውስ) እኔ ሰውን ከሚቅጨለጨል ሸክላ ከሚገማም ጭቃ እፈጥራለሁ (ፍጥረቱን) ባስተካከልኩትና በውስጡ ከመንፈሴ በነፋሁበትም ጊዜ ለእርሱ ሰጋጆች ኾናችሁ ውደቁ፡፡ መላእክትም መላውም ተሰብስበው ሰገዱ፡፡ ኢብሊስ (ዲያብሎስ) ብቻ ሲቀር ከሰጋጆቹ ጋር ከመሆን እምቢ

**አለ፡፡ (አላህም)፡- ኢብሊስ ሆይ ከሰጋጆቹ ጋር የማትሆነው ላንተ ምን ምክንያት አለህ አለው፡፡ ከሚቅጨለጨል ሸክላ ከግም ጭቃ ለፈጠርከው ሰው ልሰግድ አይገባኝም አለ፡፡ <u>(አላህ) አለው ከርሷም ውጣ አንተ የተባረርክ ርጉም ነህና፡፡ ባንተ ላይም እስከፍርዱ ቀን ድረስ ርግማን አለብህ ፡</u>**

وَلَقَدْ خَلَقْنَا الْإِنسَانَ مِن صَلْصَالٍ مِّنْ حَمَإٍ مَّسْنُونٍ وَالْجَانَّ خَلَقْنَاهُ مِن قَبْلُ مِن نَّارِ السَّمُومِ وَإِذْ قَالَ رَبُّكَ لِلْمَلَائِكَةِ إِنِّي خَالِقٌ بَشَرًا مِّن صَلْصَالٍ مِّنْ حَمَإٍ مَّسْنُونٍ فَإِذَا سَوَّيْتُهُ وَنَفَخْتُ فِيهِ مِن رُّوحِي فَقَعُوا لَهُ سَاجِدِينَ فَسَجَدَ الْمَلَائِكَةُ كُلُّهُمْ أَجْمَعُونَ إِلَّا إِبْلِيسَ أَبَىٰ أَن يَكُونَ مَعَ السَّاجِدِينَ قَالَ يَا إِبْلِيسُ مَا لَكَ أَلَّا تَكُونَ مَعَ السَّاجِدِينَ قَالَ لَمْ أَكُن لِّأَسْجُدَ لِبَشَرٍ خَلَقْتَهُ مِن صَلْصَالٍ مِّنْ حَمَإٍ مَّسْنُونٍ قَالَ فَاخْرُجْ مِنْهَا فَإِنَّكَ رَجِيمٌ

ሙፈሲር ኢብን ካሲር ለዚህ የቁርአኑ አንቀጽ ማብራሪያ /ተፍሲር/ ሲያዘጋጁ ለሰጡት ሃሳብ ማጠናከሪያ የሚከተለውን ሀዲስ አያይዘው አቅርበው እናገኛለን፡-

**ተፍሲር ኢብን ካሲር ሱረቱል አል-ሒጅር 15 ፡ 34-37**

ሳኢድ ቢን ጁቤይር ሲናገር አላህ ኢብሊስን <u>**(ሰይጣንን) በረገመው ጊዜ መልኩ ከመላዕክት ወደተለየ መልክ ተቀየረ፣ ድምጹም እንደ ደወል ድምጽ ሆነ**</u>፡፡ በዚህም ምድር ላይ እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ የሚሰማ ማንኛውም የደወል ድምጽ የዛው የሰይጣን ድምጽ አካል ነው፡፡ ኢብን አቢ ሃቲም ያስተላለፈው ሃዲስ ነው

ከዚህ በመነሳት ሐዲሳቱን ስንመረምር ደወልና ሰይጣን ያላቸው ግንኙነት ምን እንደሚመስል ከነቢዩ ሙሃመድ አንደበት ሰምተው ሱሃባዎቹ ያስተላለፉትን ደጋግመው ዘግበው እናገኛለን ፡፡ ከዛ እስቲ አንድ ሁለት ላስነብባችሁ፡-

**ሳሂህ ሙስሊም 24 ፡ 5279**
የአላህ መልእክተኛ ሲናገሩ እንዲህአሉ፡- <u>**ደወል የሰይጣን የሙዚቃ መሳሪያ ነው**</u>፡፡ **አቡ ሁሬይራ የዘገቡት ሃዲስ ነው**

**ሳሂህ ሙስሊም 24 ፡ 5277**
የአላህ መልእክተኛ ሲናገሩ፡- መልአክ <u>**ደወልና ውሻ ይዘው ከሚጓዙ ጋር**</u> አብሮ አይሄድም፡፡ **አቡ ሁሬይራ የተናገሩት ሃዲስ**

**ሱና አቡ ዳውድ 34 ፡ 4218**
ኢብን አዝ-ዙቤይር ሴት አገልጋዩን ሴት ልጁን ይዛ ወደ ኡመር እንድትሄድ ነገራት ልጅቷን እግሯ ላይ ደወል ያለበት አልቦ እንዳደረገች ወሰደቻት፡፡ ኡመርም የአላህ መልእክተኛ <u>**ከእያንዳንዱ ደወል ጋር ሰይጣን**</u>

**<u>አለ ሲሉ ሰምቻለሁ</u> አለና አልቦውን ቆራርጦ ጣለው ፡፡ ኡመር ኢብን ኸታብ የተናገሩ ሃዲስ ነው**

2. ሰይጣን አላህ ለአደም ስገድ ሲለው ባለመታዘዙ ተረግሞ ከገነት በተባረረ ጊዜ በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ፍጹም ጥላቻ ተሞልቶ የመጀመሪያው በእነርሱ ላይ በጠላትነት የተነሳ አካል እንደ ሆነ ቁርአንና የነቢዩ ሐዲሳት በአንድነት ይገልጻሉ፡፡ አላህም እንዲህ በማለት የሰው ልጆችን በቁርአኑ አስጠንቅቋል፡-

**ሱረቱል አል-ኢስራእ 17 ፡ 62**
**ንገረኝ ይህ ያ በኔላይ ያበለጥከው ነውን ; እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ ብታቆየኝ <u>ዘሮቹን ጥቂቶች ሲቀሩ ወደ ስህተት በእርግጥ እስባቸዋለሁ ፡፡</u>**

قَالَ أَرَأَيْتَكَ هَٰذَا الَّذِي كَرَّمْتَ عَلَيَّ لَئِنْ أَخَّرْتَنِ إِلَىٰ يَوْمِ الْقِيَامَةِ لَأَحْتَنِكَنَّ ذُرِّيَّتَهُ إِلَّا قَلِيلًا

**ሱረቱል አል-አንአም 6 ፡ 142**

ከለማዳ እንስሳት የሚጫኑትንና የማይጫኑትን (ፈጠረ) አላህ ከሰጣችሁ ሲሳይ ብሉ የሰይጣንንም እርምጃዎች አትከተሉ **<u>እርሱ ለናንተ ግልጽ ጠላት ነውና ፡፡</u>**

وَمِنَ الْأَنْعَامِ حَمُولَةً وَفَرْشًا ۚ كُلُوا مِمَّا رَزَقَكُمُ اللَّهُ وَلَا تَتَّبِعُوا خُطُوَاتِ الشَّيْطَانِ ۚ إِنَّهُ لَكُمْ عَدُوٌّ مُّبِينٌ

**ሱረቱል አል-በቀራህ 2 ፡ 168**
እላንተ ሰዎች ሆይ! በምድር ካለው ነገር የተፈቀደ ጣፋጭ ሲሆን ብሉ የሰይጣንንም እርምጃዎች አትከታተሉ **<u>እርሱ ለናንተ ግልጽ ጠላት ነው ፡፡</u>**

يَا أَيُّهَا النَّاسُ كُلُوا مِمَّا فِي الْأَرْضِ حَلَالًا طَيِّبًا وَلَا تَتَّبِعُوا خُطُوَاتِ الشَّيْطَانِ ۚ إِنَّهُ لَكُمْ عَدُوٌّ مُّبِينٌ

**ሱረቱል አል-በቀራህ 2 ፡ 208**
እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ሁላችሁ በመታዘዝ ውስጥ ግቡ የሰይጣንንም ርምጃዎች አትከታተሉ **<u>እርሱ ለናንተ ግልጽ ጠላት ነውና</u>**

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا ادْخُلُوا فِي السِّلْمِ كَافَّةً وَلَا تَتَّبِعُوا خُطُوَاتِ الشَّيْطَانِ ۚ إِنَّهُ لَكُمْ عَدُوٌّ مُّبِينٌ

# ሰይጣን እና ተቀዳሚ አላማው

ከላይ እንዳነበባችሁት ሰይጣን አላህ ለአደም ስገድ ሲለው አሻፈረኝ በማለቱ /ትእዛዙ ትክክል ነው አይደለም፣ እንዲህ አይነት ትእዛዝ አላህ ያዛል ወይንስ አያዝም የሚለውን ብርቱ ጥያቄ ሳናነሳ ማለቴ ነው/ ምህረት በሌለው እርግማን ለዘለአለም ተረግሞ ከገነት ተባሯል፡፡ ሰይጣን ይህንን የመሰለ የፍርድ ውሳኔ በተላለፈበት ወቅት አላህን የለመነው የሰውን ልጆች እርሱን ከመከተል ለመመለስና ወደ ጀሃነመ እሳት ለመውሰድ ስለሚፈልግ ጊዜ እንዲሰጠው ብቻ ነበር እንጅ ጥፋተኛነቱን አምኖ ተውበት በማድረግ /በሃጢያቱ ተጸጽቶ/ እርሱና ዘሮቹ ከገሃነመ እሳት የሚተርፉበትን መንገድ እንዲመራቸው አልነበረም፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር ብቻ እለምንሃለሁ አለ፡- "ገሃነምን በሰው ልጆች እስክሞላ ድረስ ጊዜ እንድትሰጠኝ፡፡" ሰይጣን ለአላህ ያቀረበውን የልመናውን ቃል እስኪ ከቁርአኑ ውስጥ እንመልከት፡-

**ሱረቱል አል-ሂጅር 15 ፡ 35-39**

ባንተ ላይም እስከ ፍርዱ ቀን ድረስ ርግማን አለብህ፡፡ ጌታዬ ሆይ <u>እንግዲያውስ (ሰዎች)</u> <u>እስከሚቀሰቀሱበት ቀን ድረስ አቆየኝ አለ</u>፡፡ (አላህም) አለ፡- <u>አንተ ከሚቆዩት ነህ</u> እስከ ታወቀው ወቅት ቀን ድረስ (ኢብሊስም) አለ፡- <u>ጌታየ ሆይ እኔን በማጥመምህ ይሁንብኝ</u> <u>ለነርሱ በምድር ላይ (ኃጢያትን) እሸልምላቸዋለሁ መላቸውንም አጠማቸውም አለሁ</u>

وَإِنَّ عَلَيْكَ اللَّعْنَةَ إِلَىٰ يَوْمِ الدِّينِ قَالَ رَبِّ فَأَنظِرْنِي إِلَىٰ يَوْمِ يُبْعَثُونَ قَالَ فَإِنَّكَ مِنَ الْمُنظَرِينَ إِلَىٰ يَوْمِ الْوَقْتِ الْمَعْلُومِ قَالَ رَبِّ بِمَا أَغْوَيْتَنِي لَأُزَيِّنَنَّ لَهُمْ فِي الْأَرْضِ وَلَأُغْوِيَنَّهُمْ أَجْمَعِينَ

**ሱረቱል አል-አዕራፍ 7 ፡ 14-17**

<u>እስከሚቀሰቀሱበት ቀን አቆየኝ አለ አንተ ከሚቆዩት ነህ አለው፡፡ ስለአጠመምከኝም ለነርሱ በቀጥተኛው መንገድ ላይ በእርግጥ እቀመጥባቸዋለሁ አለ</u>፡፡ ከዚያም ከስተፊቶቻቸው ከኋላቸውም ከቀኛቸውም ከግራቸውም በእርግጥ እመጣባቸዋለሁ አብዛኞቻቸውም አመስጋኞች ኾነው አታገኛቸውም (አለ)፡፡

قَالَ أَنظِرْنِي إِلَىٰ يَوْمِ يُبْعَثُونَ قَالَ إِنَّكَ مِنَ الْمُنظَرِينَ قَالَ فَبِمَا أَغْوَيْتَنِي لَأَقْعُدَنَّ لَهُمْ صِرَاطَكَ الْمُسْتَقِيمَ ثُمَّ لَآتِيَنَّهُم مِّن بَيْنِ أَيْدِيهِمْ وَمِنْ خَلْفِهِمْ وَعَنْ أَيْمَانِهِمْ وَعَن شَمَائِلِهِمْ ۖ وَلَا تَجِدُ أَكْثَرَهُمْ شَاكِرِينَ

**ሱረቱል ሷድ 38 ፡ 79- 82**

**<u>ጌታዬ ሆይ እስከሚቀሰቀሱበት ቀን ድረስ አቆየኝም</u>** አለ (አላህም) አለው፡- **<u>አንተ ከሚቆዩት ነህ</u>** እስከ ታወቀው ወቅት ቀን ድረስ፡፡ (እርሱም) አለ፡- **<u>በአሸናፊነትህ ይሁንብኝ በመላ አሳስታቸዋለሁ፡፡</u>**

قَالَ رَبِّ فَأَنظِرْنِي إِلَىٰ يَوْمِ يُبْعَثُونَ قَالَ فَإِنَّكَ مِنَ الْمُنظَرِينَ إِلَىٰ يَوْمِ الْوَقْتِ الْمَعْلُومِ قَالَ فَبِعِزَّتِكَ لَأُغْوِيَنَّهُمْ أَجْمَعِينَ

**ሱረቱል አል-ኢስራእ 17 ፡ 62**

ንገረኝ ይህ ያ በኔላይ ያበለጥከው ነውን? **<u>እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ ብታቆየኝ ዘሮቹን ጥቂቶች ሲቀሩ ወደ ስህተት በእርግጥ እስባቸዋለሁ</u>**፡፡

قَالَ أَرَأَيْتَكَ هَٰذَا الَّذِي كَرَّمْتَ عَلَيَّ لَئِنْ أَخَّرْتَنِ إِلَىٰ يَوْمِ الْقِيَامَةِ لَأَحْتَنِكَنَّ ذُرِّيَّتَهُ إِلَّا قَلِيلًا

አላህ ሰይጣን ላቀረበውን ልመና ተቀብሎ ምላሽ በሰጠበት ወቅት ለሰይጣንና ለሰው ልጆች የሚከተለውን ጨምሮ ተናግሮ ቁርአን ውስጥ አንመለከታለን፡-

**ሱረቱል ፋጢር 35 ፡ 6**

ሰይጣን ለናንተ ጠላት ነው ስለዚህ **<u>ጠላት አድርጋችሁ ያዙት ተከታዮቹን የሚጠራው ከእሳት ጓዶች እንዲሆኑ ብቻ ነው</u>**፡፡

إِنَّ الشَّيْطَانَ لَكُمْ عَدُوٌّ فَاتَّخِذُوهُ عَدُوًّا ۚ إِنَّمَا يَدْعُو حِزْبَهُ لِيَكُونُوا مِنْ أَصْحَابِ السَّعِيرِ

**ሱረቱል አል-አዕራፍ 7 ፡ 18**

የተጠላህ ብራሪ ስትሆን ከርሷ ውጣ **<u>ከነርሱ የተከተለህ ከናንተ ከመላችሁ</u>** **<u>ገሃነምን</u>** **<u>በእርግጥ እሞላታለሁ፡፡</u>**

قَالَ اخْرُجْ مِنْهَا مَذْءُومًا مَّدْحُورًا ۖ لَّمَن تَبِعَكَ مِنْهُمْ لَأَمْلَأَنَّ جَهَنَّمَ مِنكُمْ أَجْمَعِينَ

**ሱረቱል አል-ሒጅር** 15 ፡ 43

**ገሃነምም (ለርሱና ለተከተሉት) ለመላውም በእርግጥ ቀጠሯቸው ናት፡፡**

لَهَا سَبْعَةُ أَبْوَابٍ لِّكُلِّ بَابٍ مِّنْهُمْ جُزْءٌ مَّقْسُومٌ

**ሱረቱል አል-ኢስራእ** 17 ፡ 63-64

**(አላህም) አለው፡- ሂድ ከነሱም የተከተለህ ገሃነም የተሞላች ቅጣት ስትሆን ፍዳችሁ ናት፡፡ ከነሱ የቻልከውንም ሰው በድምጽህ አታል በነሱም ላይ በፈረሰኞችህ በእግረኞችህም በልጆቻቸውም ተጋራቸው ተስፋ ቃልም ግባላቸው**

قَالَ اذْهَبْ فَمَن تَبِعَكَ مِنْهُمْ فَإِنَّ جَهَنَّمَ جَزَاؤُكُمْ جَزَاءً مَّوْفُورًا وَاسْتَفْزِزْ مَنِ اسْتَطَعْتَ مِنْهُم بِصَوْتِكَ وَأَجْلِبْ عَلَيْهِم بِخَيْلِكَ وَرَجِلِكَ وَشَارِكْهُمْ فِي الْأَمْوَالِ وَالْأَوْلَادِ وَعِدْهُمْ ۚ وَمَا يَعِدُهُمُ الشَّيْطَانُ إِلَّا غُرُورًا

**አላህ በመጨረሻ በሙታን ትንሳኤ ወቅት ሰይጣንንና ዘሮቹን በነገሩ ጅማሬ በሰው ልጆች ላይ ያስተላለፉትን የጠላትነት አዋጅ እንዳቀዱት ማከናወናቸውን ተመልክቶ ምን እንደሚላቸው ሲገልጽ፡-**

**ሱረቱል አል-አንአም** 6 ፡ 128

**ሁሉንም የሚሰበስባቸውንም ቀን (አስታውስ) <u>ያጋንንት ጭፍሮች ሆይ ከሰዎች (ጭፍራን በማጥመም) በእርግጥ አበዛችሁ (ይባላሉ) ከሰዎችም የኾኑት ወዳጆቻቸው</u>፡- ጌታችን ሆይ ከፊላችን በከፊሉ ተጠቀምን ያንንም ለኛ የወሰንክልንን ጊዜያችንን ደረስን ይላሉ እሳት አላህ የሻው ጊዜ ሲቀር በውስጧ ዘውታሪዎች ስትኾኑ መኖሪያችሁ ናት ይላቸዋል ጌታህ ጥበበኛው አዋቂ ነውና**

وَيَوْمَ يَحْشُرُهُمْ جَمِيعًا يَا مَعْشَرَ الْجِنِّ قَدِ اسْتَكْثَرْتُم مِّنَ الْإِنسِ ۖ وَقَالَ أَوْلِيَاؤُهُم مِّنَ الْإِنسِ رَبَّنَا اسْتَمْتَعَ بَعْضُنَا بِبَعْضٍ وَبَلَغْنَا أَجَلَنَا الَّذِي أَجَّلْتَ لَنَا ۚ قَالَ النَّارُ مَثْوَاكُمْ خَالِدِينَ فِيهَا إِلَّا مَا شَاءَ اللَّهُ ۗ إِنَّ رَبَّكَ حَكِيمٌ عَلِيمٌ

አላህ ለሰይጣን ልመና ያንን የመሰለ ምላሽ መስጠቱ የሚገርም ቢሆንም፣ ከዛው ጋር በማያያዝ በሌላ አንቀጽ ላይ አንድ የማይባስ ማስጠንቀቂያ እንደ ሰጠው ሰይጣንም የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ ላይዳፈር በመስማማት ምላሹን ሲሰጥ እንመለከታለን፡፡ ሰይጣን ላይጥሰው አሜን ብሎ የተቀበለውን የማስጠንቀቂያውን ቃል ከሚከተሉት የቁርአን አያቶች ላይ በግልጽ ሰፍሯል፡-

**ሱረቱል አል-ኢስራእ 17 ፡ 65**

**<u>ባሮቼ በነሱ ላይ ፈጽሞ ላንተ ስልጣን የለህም</u> መጠጊያ በጌታህ በቃ፡፡**

إِنَّ عِبَادِي لَيْسَ لَكَ عَلَيْهِمْ سُلْطَانٌ ۚ وَكَفَىٰ بِرَبِّكَ وَكِيلًا

**ሱረቱል አል ሂጅር 15 ፡ 42**

**<u>እነሆ ባሮቹ በነርሱ ላይ ስልጣን የለህም</u> ከጠማሞቹ የተከተለህ ሰው ብቻ ሲቀር፡**

إِنَّ عِبَادِي لَيْسَ لَكَ عَلَيْهِمْ سُلْطَانٌ إِلَّا مَنِ اتَّبَعَكَ مِنَ الْغَاوِينَ

**ሱረቱል ሷድ 38 ፡ 83**

**ከነርሱ ምርጥ የሆኑት ባሮችህ ብቻ ሲቀሩ፡፡**

إِلَّا عِبَادَكَ مِنْهُمُ الْمُخْلَصِينَ

ለሰይጣን ብቻ ሳይሆን ለነቢዩም የሚከተለውን ብሏቸዋል፡-

**ሱረቱል አል-ነህል 16 ፡ 98-100**

**ቁርአንን ባነበብህ ጊዜ ርጉም ከሆነው ሰይጣን በአላህ ተጠበቅ እርሱ በነዚያ ባመኑትና በጌታቸው ላይ በተጠጉት ላይ ለርሱ ስልጣን የለውምና፡፡ ስልጣኑ**

በነዚያ በሚታዘዙት ላይና በነዚያም እነርሱ በርሱ (ምክንያት) አጋሪዎች በሆኑት ላይ ብቻ ነው

فَإِذَا قَرَأْتَ الْقُرْآنَ فَاسْتَعِذْ بِاللَّهِ مِنَ الشَّيْطَانِ الرَّجِيمِ إِنَّهُ لَيْسَ لَهُ سُلْطَانٌ عَلَى الَّذِينَ آمَنُوا وَعَلَىٰ رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ إِنَّمَا سُلْطَانُهُ عَلَى الَّذِينَ يَتَوَلَّوْنَهُ وَالَّذِينَ هُم بِهِ مُشْرِكُونَ

ዶክተር ሳኢድ እስማኢል የተባሉ ኢስላማዊ ምሁር **ፋት አል-ቀድዋ ወአል-ቀድር** በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ አላህ የሰው ልጆችን እንዲሁም ሰይጣንንና ዘሮቹን ለምን እንደፈጠራቸውና በምድር ላይ የሚኖራቸውን ኃላፊነት ወይም ተጠያቂነት ሲጠቅሱ የሚከተለውን ነበር ያሉት፡-

"የአዳምና ዘሮቹ ተቀዳሚ ተጠያቂነታቸው በምድር ላይ በጎ የሆነውን ነገር እንዲያስፋፉ ሲሆን ሰይጣንና ዘሮቹ ጂኖች ደግሞ ክፉ የሆነውን ነገር እንዲያስፋፉ ነው፡፡ ይሁን እንጅ የአላህ ውሳኔ ለሁለቱም እኩል የሆነን የመምረጥን እድል ሰጥቷቸዋል፡፡ የሰው ልጆች ከተፈጠሩበት አላማ ተመልሰው ወደ ጥመት መሄድን መምረጥ ይችላሉ ሰይጣንና ጂኖቹም እንዲሁ ተመልሰው በአላህ መመራትን መምረጥ ይችላሉ፡፡"

FAT, AL QADA WAL QADAR, BY DR. SAEED ISMAEEL

ምንም የዶክተሩ አሳብ ከቁርአን ጋር እየተጣረሰ ቁርአንም እርስ በእርሱ እንዲጣረስ የሚያደርግ ነገር ቢታይበትም እርሱን ለጊዜው አቆይተነው በሁለቱ ወገኖች ላይ አላህ በሰጠው ኃላፊነት ላይ ትኩረታችንን እናድርግ፡፡ አላህ እነዚህን ወገኖች ሲፈጥራቸው ከሰይጣንና ከዘሮቹ የሚጠብቀውና ተጠያቂ ያደረጋቸው ለክፋት ሲሆን ሰዎችን ደግሞ መልካሙን እንዲያደርጉ መሆኑ ከዶክተሩ ብቻ ሳይሆን ከላይ ከተጠቀሱት የቁርአኑ አያቶች ላይ ለመመልከት ችለናል፡፡ እነዚህ ፍጥረታት ለፈጣሪያቸው ለአላህ መገዛታቸውን የሚያረጋግጡት ይህንን የሚጠበቅባቸውን ፈጽመው ከተገኙ ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ሰይጣን ክፋትን በማንገስ መገዛቱን ሲያሳይ፣ የሰው ልጅ ደግሞ መልካም የሆነውን ብቻ በማድረግ መገዛቱን ያሳያል ማለት ነው፡፡ ሁለቱም ወገኖች የተወሰነባቸውን ለመወጣት ሲንቀሳቀሱ በተለይ ሰይጣን የሰው ልጆችን በማጥመም ወደ ገሃነም እንዳይወስዳቸው አላህ በተለያየ ጊዜ የእርሱን መንገድ እንዲጠብቁ የሚመክሩና የሚያስጠነቅቁ ነቢያትን በየዘመናቱ ይልክ ነበር፡፡ በመጨረሻ ነቢዩ ሙሃመድ ከአላህ በነቢይነት ቁርአኑ ተሰጥቷቸው እንደተላኩ በዛን ዘመን ለነበረው ህዝብ አበሰሩ ዛሬም ይኸው ብስራት ለተለያዩ ወገኖችና ዘሮች እየተበሰረ ይገኛል፡፡ ሆኖም ማንኛውም ነቢይ ለነቢይነቱ ማስረጃ

እንደሚያቀርበው ሁሉ የእርሳቸውን ነቢይነት ለማስረገጥ የሚሰጡት ማስረጃዎች ግን የነቢይነት ተልዕኳቸው ከአላህ ዘንድ ነው ብሎ አምኖ ለመቀበል እጅግ አስቸጋሪ እንዲሆን አድርገዋል፡፡

እንግዲህ ገነት መግባት ስለምፈልግ ከሚሰጡት የነቢይነታቸው ማስረጃዎች የተነሳ ተልእኳቸውን በተመለከተ ውስጤ የተነሱትን ጥያቄዎች ለመመለስ ቁርአኑንና ሐዲሳቱን እንዲሁም በህይወት ታሪካቸው ዙሪያ የተጻፉትን የታሪክ መጽሐፍት ሳገላብጥ ከእነዚህ የእስልምና እውቅ መጽሐፍት ውስጥ ያገኘሁት መልስ ግን እንደተባለው ሳይሆን ነቢዩ ሙሃመድም ሆኑ ቁርአን የአላህ መልዕክትና መልእክተኛ አይደሉም የሚል ሆኗል፡፡ እናንተም ይህንን ታረጋግጡ ዘንድ፣ ተሳስቼም ከሆነ በአድራሻዬ እርማታችሁን ታደርሱኝ ዘንድ፣ ትክክልም ከሆንኩ መንገዳችሁን ለትመርመር እንዲረዷችሁ የነቢዩን የተልእኮ አጀማመር፣ ለማን እንደተላኩና መልእክቱ በምን ሁኔታ ይደርሳቸው እንደነበር፣ የሚያትቱትን ሐዲሳትና የቁርአኑን አያቶች ላስነብባችሁ፡፡ ከዛም በመቀጠል የነፍሴን ጥያቄዎች አቀርባለሁ፡-

# ነቢዩ ሙሐመድ ስለ ተልዕኳቸው አጀማመር ሲናገሩ፡-

የነቢዩ ሙሐመድ ተልዕኮ የተጀመረው ማንኛውም የቁሬይሽ ጎሳ አባላት ያደርጉት እንደነበረው ለማድረግ በሂራ ዋሻ ውስጥ ለተመስጦ ለአንድ ወር በተቀመጡበት ወቅት እንደ ነበር ይነገራል፡፡ በወርሃ ረመዳን በወሩ የመጨረሻ ቀናት ላይ ድንገት በሌሊት አንድ ማንነቱንና ምንነቱን የማያውቁት አካል መጥቶ **ሱረቱል አል-አለቅ** 96 ፡ 1-5 ያለውን አያት እንዲቀሩ እንዳስገደዳቸውና አልተማርኩም እንኳን ሲሉት ከምንም ሳይቆጥር ፊደል ያልቆጠረን ሰው እንዴት ያደርጋቸው እንደ ነበር ሚስታቸው አኢሻ በሐዲሳቸው ተናግራለች፡፡ እስኪ ሐዲሱን ላስነብባችሁ፡-

**ተፍሲር ኢብኑ ካሲር ሱረቱል አል-አለቅ** 96 ፡ 1-5

> በዋሻው ሳሉ መልአኩ ወደ እርሳቸው መጣና አንብብ አላቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛ ሲናገሩ እኔም ማንበብ አልችልም ስል መለስኩለት አሉ፡፡ ከዛም መልአኩ ጨመቀኝና የምሞት እስኪመስለኝ ድረስ አረገጠኝ ከዛም ለቀቀኝና አንብብ አለኝ እኔም መልሼ ማንበብ አልችልም አልኩት፡፡ እርሱም ለሁለተኛ ጊዜ ጨመቀኝ እኔም የምሞት እስኪመስለኝ ድረስ አረገጠኝ፣ ከዛም እንደገና ለቀቀኝና አንብብ አለኝ፡፡ እኔም ማንበብ

አልችልም አልኩት፣ አሁንም ለሶስተኛ ጊዜ እየጨመቀ እረገጠኝ፣ ከዛም ለቀቀኝና አለኝ፡

**ሱረቱል አል-አለቅ 96 ፡ 1-5**
አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም፡፡ ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)፡፡ አንብብ ጌታህ በጣም ቸር ሲሆን ያ በብዕር ያስተማረ ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲሆን፡፡

እነዚህን አንቀጾች ይዘው ልባቸው እየተንቀጠቀጠ ወደ ቤት ወደ ኸድጃ መጡና ሸፍኑኝ ሸፍኑኝ አሉ፡፡ እነርሱም ፍርሃቱ እስከሚለቃቸው ድረስ ሸፈኗቸው፡፡ ከዛም በኋላ የተፈጠረውን ሁሉ ለኸድጃ ነገሯት እንዲህም አሏት ፈርቻለሁ የሆነ ነገር ሳልሆን አልቀረሁም፡፡ ኸድጃም ከዋራቃ ኢብን ናኡፋል ጋር አገናኘቻቸው፡፡ እርሱም እስልምና ገና ሳይመጣ ክርስትናን የተቀበለና አላህ እንዲጽፍ የፈቀደለትን ያክል ወንጌልን ከሂብሩ ወደ አረብኛ ተርጉሞ መጽሃፍ የጻፈ ሰው ነው፡፡ ዋራቃ በጊዜው ሽምግሎና የአይን ብርሃኑን አጥቶ ነበር፡፡ ኸድጃም ዋራቃን አጎቴ የወንድምህን ልጅ ታሪኩን አድምጠው አላቸው፡፡ ዋራቃም የወንድሜ ልጅ ሆይ ያየኸው ምንድን ነው? ሲል ጠየቃቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛም ያዩትን ሁሉ ገለጹለት ዋራቃም እርሱማ አላህ ወደ ሙሴ ልኮት የነበረው አን-ናሙስ ገብርኤል ነው አላቸው፡፡

## ነቢዩ ሙሐመድ ለማን እንደተላኩ፡-

ነቢዩ ሙሃመድ ነቢይ ሆነው ከአላህ እንደተላኩ ሲያበስሩ የመልዕክቱ ተደራሾች እነማን ናቸው ሲባል አላህ በቁርአኑ አንቀጾች <u>ለዓለማት</u> እንደሆነ ተናግሯል፡፡ ዓለማት የሚለው ቃል አላህ ለምን የመጀመሪያ አሳቡን እንደለወጠ ባይታወቅም ሰዎችንና ሰይጣናትን እንደሚያጠቃልል የቁርአኑ ሙፈሲሮች ይናገራሉ፡፡ በሱረቱል አል-ጂን ላይም እነዚሁ ሰይጣናት ተልዕኳቸውንና ከአላህ የተቀበሉትን ኃላፊነት በሚቃረን ሁኔታ እኛም እስልምና እውነተኛ ስለሆነ ተቀበልን ሲሉም አንብበናል፡፡ ይሁንና ቀጥዬ ስለ ነቢዩ ሙሐመድ ተልዕኮ የሚናገሩትን የቁርአኑን አንቀጾች፣ እንዲሁም የኢብን አባስና የኢብን ካሲር ተፍሲሮች ስለዚሁ ምን እንደሚሉ ላስነብባችሁ፡-

**ሱረቱል ዩሱፍ 12 ፡ 104**

በርሱ በቁርአን ላይ ምንም ዋጋ አትጠይቃቸውም እርሱ **<u>የዓለማት</u>** ግሳጼ እንጅ ሌላ አይደለም፡

وَمَا تَسْأَلُهُمْ عَلَيْهِ مِنْ أَجْرٍ ۚ إِنْ هُوَ إِلَّا ذِكْرٌ لِّلْعَالَمِينَ

(104. And no reward you ask of them for it; it (the Qur'an) is no less than a Reminder unto the `Alamin (men and Jinn).) **ተፍሲር ኢብን ካሲር**

[12:104]
(Thou askest them) O Muhammad (no fee) no payment (for it) for the profession of monotheism. (It is) i.e.the Qur'an (naught else than a reminder) an admonition (unto the peoples) **unto the jinn and humans.** **ተፍሲር ኢብን አባስ**

**ሱረቱል አል-አንቢያ 21 ፡ 107**

(ሙሃመድ ሆይ !) **ለዓለማት** እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም ፡፡

وَمَا أَرْسَلْنَاكَ إِلَّا رَحْمَةً لِّلْعَالَمِينَ

(107. And We have sent you (O Muhammad ) not but as a mercy for the `Alamin.) **ተፍሲር ኢብኑ ካሲር**

[21:107]
(We sent thee) O Muhammad (not save as a mercy) that shields from chastisement (for the peoples) from among the jinn, humans and all those who believe in you; it is also said that mercy here means blessing. **ተፍሲር ኢብን አባስ**

# መልእክቱን በምን ሁኔታ እየመጣላቸው ይቀበሉ እንደነበር ሲናገሩ፡-

ቀጥዬ አኢሻ ነቢዩ ሙሐመድ ራዕይ እንዴት እየመጣላቸው እንደሚቀበሉ ከሱሃባዎቻቸው /ባልደረቦቻቸው/ አንዱ ጠይቋቸው ምላሽ ሲሰጡ የሰማችውንና የተናገረችውን ሐዲስ ላስነብባችሁ፡፡ ሐዲሱ በተለያዩ ሳሂህ /ትክክለኛ/ በሆኑ የሐዲስ መጽሐፍቱ ውስጥ በሰፊው ተዘግቦ ይገኛል እንዲህ ይላል፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ 54 ፡ 438 ቅጽ 4**

አል-ሃሪስ ቢነ ሂሻም ነቢዩን እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፡- ራዕዩ ሲወርድ የሚመጣለዎት በምን ሁኔታ ነው? እርሳቸው ሲመልሱም መልአኩ አንዳንድ ጊዜ **የደወል ድምጽ** **በሚመስል ድምጽ እየተናገረ ይመጣል፤** ይህ አይነቱ የራዕዩ አወራረድ ለእኔ በጣም ልቋቋመው የማልችለው ከባዱ አይነት ነው፡፡ ትቶኝ ከሄደ በኋላ መልአኩ የነገረኝን አስታውሰዋለሁ፡፡ አንዳንዴ መልአኩ ሰው በመምሰል ወደ እኔ ይመጣና ያናግረኛል እኔም ምን እንዳለኝ እረዳለሁ አስታውሰዋለሁም፡፡ አኢሻ አክላም **እርሱ በእርሳቸው ላይ በወረደ ጊዜ ከባድ ብርድ እንደሚያንቀጠቅጠው ሰው ይንቀጠቀጣሉ ትቷቸው ሲሄድ ደግሞ ግንባራቸው ላብ በላብ ይሆናል፡፡** አኢሻ የዘገበችው ሐዲስ ነው

# ነቢዩ ሙሐመድ ስለራሳቸውና ስለተከታዮቻቸው ሲናገሩ፡-

ጊዜው ሱረቱል አል-ፈለቅና ሱረቱል አል-ናስ የወረዱበት ሰአት ነበር ፡፡ ከእነዚህ ሁለት ሱራዎች በፊት መካ ላይ 19 ሱራዎች ከወረዱ በኋላ በ20ኛ እና 21ኛ ደረጃ ላይ የወረዱ ሱራዎች ናቸው፡፡ የሩቅያህ ወይንም የመተት ሱራዎች ተብለው በሌላ ስምም ይጠራሉ፡፡ ይህንን ስያሚ ለምን አገኙ የሚል ጥያቄ ያነሱ ይሆናል፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡- በዛን ወቅት **ላቢድ ቢን አሳም** የሚባል አይሁዳዊ በነቢዩ ሙሐመድ የራሳቸው ጸጉርና በማበጠሪያቸው ላይ አስማት ያደርግምባቸውና ለአንድ አመት ያክል በጸና ይታመማሉ፤ ህመም ከተባለ ማለቴ ነው፡፡ ያኔ በዚሁ በተደረገባቸው አስማት ምክንያት ከሚስቶቻቸው ጋር ወሲብ የሚፈጽሙ እየመሰላቸው ከማያውቁት አካል ጋር ወሲብ ሲያስፈጽማቸው ይታይ ነበር፡፡ ይህንን ዝም ብዬ የምናገር እንዳይመስላችሁ **ሳሂህ አል-ቡኻሪ** 71 ፡ 660 **ቅጽ** 7 ላይ በተጨማሪ **አስባቡ አል-ኑዙል ሱራ** 113 **እና** 114 ላይ መመልከት ትችላላችሁ፤ ከሐዲሱ ቀንጭቤ ላስነብባችሁ፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ** 71 ፡ 660 **ቅጽ** 7

አይሻ ስትናገር፡- የአላህ መልእክተኛ ላይ ድግምቱ ሰርቶባቸው፣ ከሚስቶቻቸው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሲፈጽሙ እንደሚያደርጉት እንዲሁ ብቻቸውን ያደርጉ ጀመር፡፡ እርሳቸው ከሚስታቸው ጋር እየፈጸሙ ይመስላቸዋል፣ ግን አልነበረም፡፡ ሌላዋ ሚስታቸው ሶፍያም እንዲህ አይነት ተግባር የሚያስተጽመው በጣም አደገኛው የድግምት አይነት ነው አለች፡፡

ከዚህ ድግምት ገብርኤል ሩቅያህ /መተት/ አድርጎላቸው ተፈወሰኩ ባሉበት ወቅት በዙሪያቸው ለተሰበሰቡት ሱሃባዎች አንድ ነገር አሏቸው እናንተ ሁላችሁ ሰይጣን አለባችሁ፡፡ ምን ይህ ብቻ እናንተው ከሐዲሱ አንብቡ እነሆ ፡-

**ሳሂህ ሙስሊም** 39 ፡ 6757

የአላህ መልእክተኛ ሲናገሩ እንዲህ አሉ፡- ከእናንተ መካከል ሰይጣን ያልተመደበበት የለም፡፡ ሱሃባዎቹም የአላህ መልእክተኛ ሆይ በእርሰዎም ላይ ሰይጣን ተመድቦበዎታልን? ብለው ጠየቁ ሲመልሱ አዎን! ተመድቦብኛል ነገር ግን አላህ በእርሱ ላይ እረዳኝና ተቃወምኩት ከሃይሉ እኔ ነጻ ነኝ <u>**አሁን የሚያዘኝ**</u> ወደ መጥፎ ስራ ሳይሆን ወደ መልካም ስራ ነው፡፡ አብዱላህ ኢብን መሱድ የዘገበው ሐዲስ ነው

**ሐዲስ ሚሽካት አል- ሙሳቢሃ ምዕ** 27 **ክፍ** 19 **ሃቁ** 131 **ቅጽ** 2

**ባሏ** ሳይኖር ሴትን አትጎብኙ ምክንያቱም ሰይጣን ደም በደም ስር እንደሚዘዋወር እንዲሁ በውስጣችሁ ይሯሯጣልና አሉ፡፡ እኛም የአላህ መልእክተኛ ሆይ! በእርሰዎም ውስጥ እንደኛው ይሯሯጣልን? ስንል ጠየቅናቸው፡፡ እርሳቸውም አዎን በእኔም ውስጥ ይሯሯጣል ነገር ግን አላህ በእርሱ ላይ እረዳኝና ተገዛልኝ አሉ፡፡ **ጃብር የተናገረው ሐዲስ ነው**

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ** 54 ፡ 516 **ቅጽ** 4

የአላህ መልእክተኛ ከእናንተ የትኛውም ሰው ከመኝታው ሲነሳ ውዱ ያድርግ አፍንጫው ውስጥ ውሃ እያስገባ እያስወጣ ሶስቴ በመደጋገም ይጠበው፡፡ ምክንያቱም ሰይጣን በአፍንጫው የላይኛው ክፍል ሌሊቱን ሙሉ አድሮ ሊሆን ይችላልና አሉ፡፡ **አቡ ሁሬይራ የዘገቡት ሐዲስ ነው**

አንዴ ነቢዩ ሙሐመድ መዲና ሲኖሩ ሳለ ደግሞ ጅኖች የአካባቢው ሙስሊሞች በሚፈጽሙባቸው ተግባር አዝነው ለነቢዩ ስሞታ አሰሙ ነቢዩም ጅኖቹ የነገሯቸውን ሰምተው ለሱሃባዎች ትእዛዝ አስተላልፈው ነበር፡፡ በዛን ጊዜ ያስተላለፉት ትዕዛዝ እንዲህ የሚል ነበር ፡-

**ሱና ጃማኢ አት-ትርሚዝ ቅጽ** 1 **ቁጥር** 18

የወንድሞቻችሁ የጅኖች ምግብ ነውና በአጥንትና በከብት ፋንድያ እስቲንጃ አታድርጉ፡፡ **አብደላ ኢብን መሱድ የተናገረው ሐዲስ ነው**

**ሱና አቡ ዳውድ 1 ፡ 39**

የጅን ባለስልጣናት ወይንም ወኪሎች ወደ ነቢዩ ሙሐመድ መጡና እንዲህ አሉ፡- ሙሐመድ ሆይ ተከታዮችህን በአጥንት በኩበት ወይንም በከሰል እራቸውን ማጽዳታቸውን /ሽንት ቤት ከተጠቀሙ በኋላ ማለት ነው/ ልትከለክላቸው ይገባል፤ እነዚህ አላህ የወሰነልን ነገሮች ናቸው፡፡ ስለዚህ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ እንዳይደረግ ተከታዮቻቸውን ከለከሉ፡ አብደላ ኢብን መሱድ የዘገበው ሐዲስ ነው

በዚህ ብቻ ያበቃ መስሏችሁ ይሆን አላበቃም ነቢዩ ሙሃመድ በእነዚህ ሰይጣናት እየተጋበዙ ከእነርሱ ጋር ወደ መኖሪያቸው እየሄዱ ብዙ ጊዜ ቁርአን ይቀሩላቸው እስልምናን ይሰብኳቸው እንደ ነበር ሱሃባዎቻቸው ዘግበዋል፡፡

**ሳሂህ ሙስሊም 4 ፡ 903**

አንድ ምሽት ከአላህ መልዕክተኛ ተከታዮች ጋር አብረን ነበርን፤ እርሳቸው ግን ጠፉብን፡፡ በሸለቆው በተራራው ሁሉ ፈለግናቸው ልናገኛቸው ግን አልቻልንም፡፡ እንዲህም አልን፡- ወይ በጅኖች ተወስደዋል ወይንም በሚስጢር ተገድለዋል አልን፡፡ ሁላችንም በብዙ ድካም መጥፎ የሆነ ምሽት አሳለፍን፡፡ ሲነጋጋ ሂን በሚባለው አካባቢ አቅጣጫ ሲመጡ አየናቸው፡፡ እኛም የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ጠፍተውብን ስንፈልግ እጅግ ደክሞን በጣም መጥፎ የሆነ ምሽት አሳለፍን አልናቸው፡፡ እርሳቸውም ከጅን ወገን የሆነና በእነርሱ የተወከለ ጅን ወደ እኔ መጣ እኔም ከእርሱ ጋር ሄድኩኝ በዛም ቁርአን ቀራሁላቸው አሉ፡፡ እኛንም ይዘውን ሄዱና የእግራቸውን ኮቴና እሳት እንድደውበት የነበረውን ቦታ አሳዩን፡፡ አብደላ ኢብኑ መሱድ የተናገረው ሐዲስ ነው

**ሱና አት-ትርሚዝ ቁጥር 3302**

የአላህ መልዕክተኛ ወደ ተከታዮቻቸው መጡና ሱረቱል አል-ረህማንን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አነበቡት፡፡ ከዛም ይህንን ሱራ በጅኖች ምሽት በጅኖች ፊት አንብቤው ነበር እነርሱ የሰጡት ምላሽ እናንተ ከሰጣችሁት ምላሽ በእጅጉ የተሻለ ነበር አሉ ፡፡

# እንግዲህ ነገሩ እንዲህ ከሆነ ለእናንተ ለአንባቢዎቼ የማነሳቸው የነፍሴ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- የመጀመሪያው ጥያቄ በተገለጠላቸው አካል ማንነት ላይ ያተኩራል፡- ራዕዩን ያመጣላቸውን አካል ማንነት ነቢዩ መጀመሪያ ማን እንደሆነ እንደማያውቁ በኋላ ግን ገብርኤል የተባለው መልአክ እንደሆነ በሰፊው ተነግሯል፡፡ እንግዲህ እንደተባለው ገብርኤል ከሆነ፡-

1. ውድ ወገኖቼ እንደተባለው ወደ ነቢዩ ሙሐመድ የመጣው መልአኩ ገብርኤል ከሆነ ድምጹ ለምን እንደ ሰይጣን ድምጽ ሆኖ ተቀየረ? ነቢዩ ሙሐመድ ራዕዩ ወደ እርሳቸው እንዴት እንደሚመጣላቸው ተጠይቀው ምላሽ በሰጡበት ሃዲስ መልአኩ የደወል ድምጽ በሚመስል ድምጽ እንደሚያናግራቸው ይህም ለእርሳቸው ከባዱ አይነት እንደ ነበር ተናግረዋል፡፡ ይህ አይነት ድምጽ ደግሞ ሰይጣን አላህን አልታዘዝ ብሎ አላህ ሲረግመው መልኩና ድምጹ ሲቀየር የተቀየረው ወደ ደወል ድምጽነት እንደነበር እራሳቸው ተናግረዋል፡፡ እንዲያውም ከላይ እንዳነበባችሁት ማንኛውም በምድር ላይ ያለ የደወል ድምጽ የሰይጣን ድምጽ አካል እንደሆነ አስረግጠው ነግረውናል፡፡ እንግዲህ እርሳቸው መጀመሪያ እንደ ገመቱት ሰይጣን ካልሆነ በስተቀር ገብርኤል ምን ብሎ የሰይጣንን ድምጽ ተውሶ እርሱን ሲሰሙም የሰይጣንን ድምጽ የሰሙ ይመስል እንዲያ መሬት ላይ ጥሎ ብርድ እንደያዘው ሰው ያንቀጠቅጣቸዋል? ለአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አይነት 23 ዓመታት የዘለቀ ስቃይ ለምን ይሆን?
2. ደውል የሚመስለው የሰይጣን ድምጽ የመባረክ ፍሬ ሳይሆን የእርግማን ፍሬ ነው፡፡ ይህን የእርግማን ፍሬ የሆነውን መጠቀም ደግሞ ለአላህ በመገዛት ላለ መልአክ የሚመጥን አይሆንም፡፡ ገብርኤል ከሆነ የራሱን ድምጽ መጠቀም ያላስፈለገውና የሰይጣንን ለመጠቀም የተገደደው ለምንድን ነው? እንዲህ ማድረግስ ማጭበርበር አይመስልም? ይህንንስ ሰይጣን ካልሆነ በስተቀር መልአኩ ገብርኤል ያደርገዋል ብላችሁ ታስባላችሁ?
3. በትክክል የተገለጠላቸው መልአኩ ገብርኤል ለመሆኑ እርግጥ ያለው ማሳመኛ ምንድን ነው? ምናልባት ዋራቃ የሰጠው ምስክርነት ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ ይህም ቢሆን አሳማኝ የማይሆንባቸው በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም አሁን ሁሉን መዘርዘር ባይቻልም ከነዛ አንዱ ምክንያት ዋራቃ ክርስቲያን መሆኑ ነው፡

4. መልአኩ ገብርኤል ከአላህ ተልኮ ወደ ሰዎች ሲመጣ የነቢዩ ሙሐመድ የመጀመሪያው ተልእኮ አይደለም ታዲያ በዚህ ጊዜ ባህሪው ለምን ተቀየረ? በሱረቱል መርይም ላይ ዘካርያስንና ማርያምን ሲያነጋግር በተረጋጋና አክብሮት በተሞላበት ሁኔታ ሆኖ ሳለ ነቢዩ ሙሃመድን ግን የሚሞቱ ከዛ ቀን በኋላ ፀሐይን የማያዩ እስከሚመስላቸው ድረስ ሲያሰቃያቸው ነበር የታየው፡፡ እንዲያውም ቤታቸው ደርሰው ኸድጃ አዕምሯቸውን እስከትቀይርላቸው ድረስ መልአክ ሳይሆን ሰይጣን ያዩ ነበር የመሰላቸው፡፡ ለዛም ነው እየተንቀጠቀጡ መጥተው ሸፍኑኝ ሸፍኑኝ ይሉ የነበረው፡፡ እስኪ ከመጽሃፍ ቅዱስ የገብርኤልና የማርያም ቃለ ምልልስ ምን ይመስል እንደ ነበር ላስነብባችሁና በነቢዩ ሙሃመድ ላይ ከፈጸመው ድርጊት ጋር ያነጻጽሩት፡-

**ሉቃስ 1 ፡ 28-38**

*መልአኩም ወደ እርሷ ገብቶ እጅግ የተወደድሽ ሆይ ሰላም ላንቺ ይሁን ጌታ ከአንቺ ጋር ነውና አንቺ የተባረክሽ ነሽ አላት፡፡ ማርያምም በንግግሩ እጅግ በጣም ደንግጣ ይህ ምን አይነት ሰላምታ ይሆን? እያለች ነገሩን ታሰላስል ጀመር፡፡ መልአኩም እንዲህ አላት ማርያም ሆይ በእግዚአብሄር ዘንድ ሞገስ አግኝተሻልና አትፍሪ፡፡ እነሆ ትጸንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ፡፡ እርሱም ታላቅ ይሆናል፣ የልዑል ልጅም ይባላል፣ ጌታ አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፣ በያዕቆብ ቤትም ለዘለአለም ይነግሳል፡፡ ማርያምም መልአኩን እኔ ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? አለችው፡፡ መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፣ ስለዚህ የሚወለደው ቅዱሱ ሕጻን የእግዚአብሄር ልጅ ይባላል፡፡ እነሆ ዘመድሽ ኤልሳቤጥም በስተርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች መካን የተባለችውም ስድስተኛ ወሯን ይዛለች ለእግዚአብሄር የሚሳነው ነገር የለምና፡፡*

5. እንግዳው አካል ባመጣው ቃል አንድ ሰው ማንበብና መጻፍ የሚችለው አላህ ካስተማረውና የቀለም ትምህርት ከወሰደ ብቻ መሆኑን እየመሰከረ፣ ምንም ባልተማሩት ሰው ላይ ካመጣው ቃል በተቃራኒ የሆነ ተግባር መፈጸሙ ለምን ይሆን? እውን ይህንን ታላቁ መልአክ ገብርኤል ይፈጽመዋል ባላችሁ ታምናላችሁ? አላህስ ቢሆን ላልተማረ ሰው እንደላከው አያውቅም ነበር? መልአክ የተባለው ይህንን የፈጸመባቸው አላህ አድርግባቸው ብሎት ነው ወይንስ በራሱ ፈቃድ? የሚገርመው ከዚህም ጊዜ በኋላ 23 ዓመት ሙሉ እየተመላለሰ ቁርአኑን ሲያስተምራቸው አንድም ቀን መጽሐፉን እንዲያነቡ

አስገድዷቸው አያውቅም፣ መጽሐፍም አልሰጣቸውም፣ ሁሉንም በቃላቸው እንዳስተማራቸው ነው የሚታወቀው፡፡ ታዲያ ይህንን አይነት ተግባር እየፈጸመ ያለው እውን መልአኩ ገብርኤል ነበር ብሎ ማመን ይቻላል? እስኪ ለመገምገም ያስችላችሁ ዘንድ አንድ ከቁርአንና አንድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አውጥቼ ላስነብባችሁ፡-

**ሱረቱል አል-አለቅ 96 ፡ 3-5**

አንብብ ጌታህ በጣም ቸር ሲሆን ያ በብዕር ያስተማረ ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲሆን፣

**ዳን 9 ፡ 21-23**

እየጸለይሁም ሳለሁ በመጀመሪያው ራዕይ አይቸው የነበረው ሰው ገብርኤል በሰርክ መስዋዕት ጊዜ በፍጥነት እየበረረ ወደ እኔ መጣ፡፡ እርሱም እንዲህ ብሎ አስረዳኝ ዳንኤል ሆይ አሁን ጥበብንና ማስተዋልን ልሰጥህ መጥቻለሁ፡ **<u>አንተ እጅግ የተወደድህ ስለሆንህ</u>** ገና መጸለይ ስትጀምር መልስ ተሰጥቶሃል፣ እኔም ይህን ልነግርህ መጣሁ፡፡ ስለዚህ መልእክቱን ልብ በል ራዕዩንም አስተውል፡፡

6. ሌላው በሳይንስ የተረጋገጠ ሃሰት ለምን ተናገረ? **በሱረቱል አል-አለቅ 96 ፡ 1-5** ከተጠቀሰው ቁጥር ሁለት **<u>‹ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው</u>›** የሚለው ሳይንስ እጅ አውጥቶ ሐሰት!! ያለው ሳይንሳዊ ስህተት ነው፡፡ እንግዲህ ቁርአን የአላህ ቃል ከሆነና ገብርኤል መልአኩ ካመጣው አላህ የሰውን የጽንስ እድገት ሁኔታ እያወቀ እንዴት ሐሰት ይናገራል? ይህንን ለማረጋገጥ ስለሰው ጽንስ እድገት /HUMAN EMBRYO/ የሚያስተምሩ መጽሃፍቶቻችሁን ማገላበጥ በቂ ነው ፡፡
7. ነቢዩ ስለ ራዕይ በተናገሩት ሐዲስ ሁኔታው ሲመረመር ለእንዲህ አይነት ተግባር ሚዛኑ የሚደፋው ወደ ሰይጣን ነው፡፡ ከዚህ አልፎ ራዕዩን ያመጣው እንዲያ አንገላትቷቸው በዛላይም የነገራቸው ቃል ሃሰተኛ ሆኖ እያለ፣ የተገለጠላቸው ገብርኤል ነው ከታባለ ሐዲሱና ቁርአኑ እንዴት ሊታረቁ ይችላሉ? ለማነጻጸር ትችሉ ዘንድ ሐዲሱን ላስነብባችሁ ይገባልና እነሆ ፡-

**ሳሂህ ሙስሊም 29 ፡ 5621**

አቡ ሁሬይራ ከአላህ መልዕክተኛ ሰምቶ ያስተላለፈው ሐዲስ ነው፡- የትንሳኤ ቀን እየተቃረበ ሲሄድ የአማኞች ራዕይ ሃሰተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ እውነተኛ ራዕይ የሚያይ በንግግሩ እውነተኛ የሆነ ሰው ብቻ ነው፡፡ የሙስሊም ራዕይ አርባ አምስት እጅ ትንቢታዊ ነው፡፡ ሶስት አይነት ራዕዮች አሉ፣ አንዱ ምልካም ራዕይ ከአላህ የሆነ ነው፡፡ **ሁለተኛው አስጨናቂ የሆነ ክፉ ራዕይ ከሰይጣን የሆነና** ሶስተኛው ከራሱ ከሰው አሳብ የሚወጣ ነው፡፡…

- ሌላው አጠያያቂ ጉዳይ የአላህ ቃልና ትዕዛዙ መጣሳቸው ነው፡- አላህ ሰይጣንን ከገነት ሲያባርረው እንዳይዳፈር የተከለከላቸውና እራሱም አምኖ የተቀበላቸው ትዕዛዛት እንደነበሩ ከላይ ማንበባችሁን ታስታውሳላችሁ፡፡ ደግሞም መከልከል ብቻ ሳይሆን የተፈቀደለት ክልልም መኖሩን አንዘነጋም፡ ፡ ይህ ሆኖ እያለ በነቢዩ ሙሃመድ የአላህ ነቢይነት ላይ ጥያቄ የሚሆነው፡-

8. አላህ ሰይጣንን እረግሞት ከገነት ሲያባርረው በባሮቹ ላይ ስልጣን እንደሌለውና እንዳይነካቸው ነግሮት እርሱም ላይነካ ምሎ መውጣቱን ቁርአን ነግሮናል፡፡ ሆኖም ግን ነቢዩ ሙሐመድ በልባቸው ሰይጣን እንዳለባቸውና ሰልሞላቸው መልካም እንዲያደርጉ እንደሚያዛቸው እንደተናገሩ አንብበናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ነቢዩ ሙሐመድ የማን ባሪያ ቢሆኑ ነው ሰይጣን መንካት አይደለም በልባቸው ቁጭ ብሎ ይህንን አድርግ ያንን አታድርግ የሚላቸው? ለንጽጽሩ ስለሚጠቅማችሁ ነቢዩ ስለ ሁለት የአላህ ባሮች የተናገሩትን ሃዲስ ላስነብባችሁ፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ** 55 ፡ 641 **ቅጽ** 4

**የአላህ መልእክተኛ** ሲናገሩ የሰማሁት፡- ከአዳም ልጆች መካከል ከማርያምና ከልጇ በስተቀር በሰይጣን ሳይነካ የሚወለድ የለም፡፡ ስለዚህ ህጻኑ ሲወለድ አምርሮ የሚያለቅሰው በሰይጣን በመነካቱ ምክንያት ነው፡ **ሳይድ ቢን አል-ሙሳ ኢያብ ከአቡ ሁሬይራ ሰምቶ የዘገበው**

የነቢዩ ሙሐመድ የልጅነት ታሪክስ ምን ይመስላል ትሉኝ ይሆን? እኔም እነሆ መልሴ እላለሁ፡-

**ሳሂህ ሙስሊም** 1 ፡ 311

ገብርኤል ወደ ሙሐመድ /ህጻኑ/ መጣ ደረቱንም በመክፈት ልቡን አወጣ፡፡ ከልቡም ውስጥ የረጋ ደም አውጥቶ ጣለው፤ ገብርኤልም ያ የሰይጣን ድርሻ የነበረ ነው አለ፡፡

9. ነቢዩ ሙሃመድ ጉልምስናቸው አይደለም ለጋ ልጅነታቸው ከሰይጣን ጋር የተነካካ ነበር፡፡ እንግዲህ ነገሩ እንዲህ ከሆነ የደወል ድምጽ እያሰማ ራዕይ የሚያቀብላቸው ገብርኤል ነበር ለማለት እንችላለን?
10. ነገሩ በእርሳቸው ቢያበቃ መልካም በነበር ሆኖም ለሱሃባዎቻቸው እንደተናገሩትና እንደ ሃዲሳቱ ዘገባ ሁሉም ሙስሊም ማህበረሰብ በአላህ የተመደበበት የራሱ ቁራኛ የሆነው ሰይጣን አለው፡፡ ይህ ንግግራቸው አላህ ቁራኛን ለማን እንደመደበ ከተናገረበት ከቁርአኑ **ከሱረቱል ሓ ሚም አል-ሰጅዳህ** 41 ፡ 25 ጋር ይጣረሳል፡፡ በዚህ ክፍል ላይ አላህ የሰይጣን ቁራኛ እንደመደበ የተናገረው የእርሱ ባልሆኑት ላይ ነበር፡፡ ሆኖም ነቢዩ ሙሐመድ ደግሞ እናንተ የአላህ ባሪያዎች ነን የምትሉት ሁላችሁ ቁራኛ ከአየሆነ ሰይጣን ላህ እንደተመደበባችሁ ነግረውናል፣ እንግዲህ እንዲህ ከሆነ ሙስሊም ወገኖቼ የማን ባሪያዎች ናችሁ ይባል? የአላህ ናችሁ እንዳንል ከቁርአኑ ባለቤትና ከነቢዩ ሙሐመድ ቃል ጋር እንጋጫለን፤ ምን ይሻላል? ደግሞስ ማን ይታመን?
11. ነቢዩ ሙሃመድ ሰይጣን ከአላህ ተመድቦባቸው ደም በሰውነት እንደ ሚዘዋወር በእርሳቸው ውስጥ እንደሚዘዋወር የነገሩን እንዳለ ሆኖ፣ የእርሳ ቸው ሰይጣን እንደሰለመላቸው ተናግረዋል ፡፡ ሰይጣን እስልምናን እንዲ ቀበል የታዘዘበት የቁርአን ክፍል የት እንደሆነ ልትነግሩን ትችላላችሁ ?
12. ቁርአኑ ላይ እንደተገለጸው አላህ ለሰው ልጆች ቁራኛ የሚሆን ሰይጣን የሚመድበው ለመልካም ሳይሆን፣ ሰዎች ወደ ጥመት ሄደው ገሃነም እንዲገቡ ቀድሞ ስለወሰነ ነው፡፡ ከላይ እንዳየነው ነቢዩ ሙሃመድ ሱሃባዎቻቸውን ሰብስበው እንደገለጹላቸው ከእራሳቸው ጀምሮ መላው ሙስሊም ማህበረሰብ ቁራኛ የሆነ ሰይጣን ከአላህ ተመድቦባቸዋል፡፡ የቁራኛ ሰይጣን አስፈላጊነት ሰዎችን የገሃነም ሰዎች እንዲያደርጉ ከሆነ አላህ በእናንተ ቁራኛ ስይጣን በመደበባችሁ ሙስሊሞች ሁሉ ላይ ገሃነምን አውጇል ማለት ነውን? አላህ ለእናንተ ሰይጣንን በቁራኛነት ያስጠጋባችሁ ከአልረህማን ወይም ከአላህ ጋር ያላችሁ ግንኙነት ምን አይነት ስለሆነ ይሆን? ሰይጣን በላዩ ላይ ቁራኛ ስለሆነበት ሰው መጨረሻ ቁርአን ምን እንደሚል ቀጥሎ ማንበብ ትችላላችሁ፡-

**ሱረቱል ሓ ሚም አል-ሰጅዳህ** 41 ፡ 25

ለነርሱ ቁራኛዎችን አዘጋጀንላቸው በፊታቸው ያለውንና በኋላቸው ያለውንም ሁሉ ለነርሱ ሸለመላቸው ከጋኔንና ከሰውም ከነሱ በፊት በእርግጥ ካለፉት ህዝቦች ጋር ኾነው ቃሉ በነርሱ ላይ ተረጋገጠባቸው እነርሱ በእርግጥ ከሳሪዎች ነበሩና፡፡

وَقَيَّضْنَا لَهُمْ قُرَنَاءَ فَزَيَّنُوا لَهُم مَّا بَيْنَ أَيْدِيهِمْ وَمَا خَلْفَهُمْ وَحَقَّ عَلَيْهِمُ الْقَوْلُ فِي أُمَمٍ قَدْ خَلَتْ مِن قَبْلِهِم مِّنَ الْجِنِّ وَالْإِنسِ ۖ إِنَّهُمْ كَانُوا خَاسِرِينَ

**ሱረቱል አል-ዝህሩፍ 43 ፡ 36-38**

ከአልረሕማን ግሳጼ የሚደናበርም ሰው ለርሱ ሰይጣንን እናስጠጋለን ስለዚህ እርሱ ለርሱ ቁራኛ ነው፡፡ እነርሱም (ተደናባሪዎቹ) ተመሪዎች መሆናቸውን የሚያስቡ ሲሆኑ እነርሱ (ሰይጣናት) ከቀጥተኛው መንገድ በእርግጥ ያግዷቸዋል፡፡ (በትንሳኤ) ወደኛ በመጣም ጊዜ (ቁራኛዬ ሆይ) በኔና ባንተ መካከል የምስራቅና የምዕራብ ርቀት በኖረ ወይ ምኞቴ ምን የከፋህ ቁራኛ ነህ ይላል፡፡

وَمَن يَعْشُ عَن ذِكْرِ الرَّحْمَٰنِ نُقَيِّضْ لَهُ شَيْطَانًا فَهُوَ لَهُ قَرِينٌ وَإِنَّهُمْ لَيَصُدُّونَهُمْ عَنِ السَّبِيلِ
وَيَحْسَبُونَ أَنَّهُم مُّهْتَدُونَ حَتَّىٰ إِذَا جَاءَنَا قَالَ يَا لَيْتَ بَيْنِي وَبَيْنَكَ بُعْدَ الْمَشْرِقَيْنِ فَبِئْسَ الْقَرِينُ

13. በመሰረቱ ሰይጣን ሃይማኖተኛ ሆነ ብሎ መናገር ከቁርአን ጋር ፈጽሞ መጋጨት ይሆናል፡፡ አላህ በእርሱ ላይ አሳቡን ወይንም ውሳኔውን ስለማይለውጥና በዘለአለም እርግማን ስለረገመው ከአላህ ጋር እንዲታረቅ የሚፈይድለት ነገር ስለማይኖር ሃይማኖተኛ መሆን ለእርሱ አስፈላጊው አይደለም፡፡ ለውጥ የሚያመጣለትና ምህረትን የሚቀበልበት እድል ቢኖረውማ ኖሮ መጀመሪያ ላይ ለአላህ ያቀረበውን ልመና ያስተካክለው ነበር፡፡ ስለዚህ ተቀዳሚ ስራው ባገኘው መንገድ ሁሉ ሰዎች ከቀጥተኛው መንገድ ወጥተው የሚገኙበትን ጎዳና ማመቻቸት ወደዛውም መሳብ ይሆናል፣ ተልዕኮውም ይህንኑ እንዲያከናውን ስለሆነ፡፡ እንግዲህ ነቢዩ ሙሐመድ እንዳሉት ሰይጣናቸው የሰለመ ከሆነና ቁርአኑ ላይ በሱረቱል አል-ጅን ላይ እንደሰፈረው ሰይጣን እስልምናን ከተቀበለ እስልምና ቀጥተኛው የአላህ መንገድ ነው ብሎ ማለት ይቻላል? ለዚህ **ሱረቱል አል-ዝህሩፍ 43 ፡ 36-38** ላይ ያለውን አንብበው ሁኔታውን ወይንም መልሰዎትን መገምገም ይችላሉ፡

14. በቁርአኑና በነቢዩ ሃዲሳት ላይ እንደተገለጸው እናንተም የተወሰነውን ከዚህ በፊት እንዳነበባችሁ ነቢዩ ሙሃመድና እናንተ ሙሰሊም ወገኖቸ ከጅኖች ጋር በቁራኛነት፣ በሃይማኖት ወንድማማችነት አንድነትና ህብረት አላችሁ፡፡ እንዲሁም በተለያዩ የቁርአኑ አያቶች ላይ አላህ በጅኖችና እነርሱን አጋርና ወዳጅ ያደረጉትን ሰዎች ሁሉ ሰብስቦ በአንድነት ገሃነም በመክተት ገሃነምን እንደሚሞላ ተናግሯል፡፡ እንግዲህ በቁርአኑ ላይ እንደሰፈረው ጅኖችና አለቃቸው ሰይጣን ሁሉም በአንድነት ተጠቅልለው ጀሃነም የሚገቡ ከሆነ ሙስሊሙ ይህንን የመሰለ ወዳጅነት ይዞ መግቢያው የት የሆናል? ቁራኛዬ ሆይ ምስራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ ከእኔ ርቀህ ቢሆን ባዮቹ እነማን ይሆኑ? እስኪ ጅኖች ቁራኛቻቸውንና የተከተላቸውን ሰው የት ድረስ እንደሚመሩት ቁርአን የተናገረውን ላስነብባችሁ፡-

**ሱረቱል ፋጢር** 35 : 6
ሰይጣን ለናንተ ግልጽ ጠላት ነው፤ ስለዚህ ጠላት አድርጋችሁ ያዙት ተከታዮቹን የሚጠራው ከእሳት ጓዶች እንዲሆኑ ብቻ ነው ፡፡
إِنَّ الشَّيْطَانَ لَكُمْ عَدُوٌّ فَاتَّخِذُوهُ عَدُوًّا ۚ إِنَّمَا يَدْعُو حِزْبَهُ لِيَكُونُوا مِنْ أَصْحَابِ السَّعِيرِ

15. አላህ ሰይጣንን ከገነት ሲያባርረው ወደ ሰው ልጆች ሂድና የቻልከውን ያክል በድምጽህ አታል በመንገዳቸውም ላይ ቁምባቸው በማለት አዞታል፡፡ ይህንን በመሰለ ተልእኮ ከአላህ ፊት የወጣው ሰይጣን አብዝቶ የሚያወራው ማደሪያ ሲያጣ ደግሞ እየመጣ የሚያድረው ከሙስሊም ወንድሞቹ ጋር እንደሆነ ከነቢዩ ንግግር ለመረዳት ችለናል፡፡ ምን ይህ ብቻ አንድ ሙስሊም ባል ከሚስቱ ጋር ወሲብ ሲፈጽም ድንገት እረስቶ ቢስሚላህ ብሎ ካልጀመረ፣ ላዳር ከመጣው ጅን ጋር አንዲቱን ሚስቱን በወሲብ ሲጋራ እንደሚያድርም ነቢዩ **በሐዲስ ሚሽካት አለ-ማሳቢህ** 9 ፡ 46 **ቅጽ** 2 ላይ ተናግረው እናገኛለን፡፡ እንግዲህ ቅርበቱና ዝምድናው ይህንን ያክል የሄደ ስለሆነ ነቢዩ ሙሐመድ አንድ ሙስሊም ሊኖረው ስለሚገባው የሌሊት ልብስ መጠን በገለጹበት ሐዲስ **የሳሂህ ሙስሊም** 24 ፡ 5190 ላይ ሰይጣን ሌሊት ሲተኛ የሚለብሰው የሌሊት ልብስ ሙስሊሞች እንዲያዘጋጁለት አዘዋል፡፡ ይህ ሁሉ ነቢዩ እራሳቸው በሐዲሳቸው የተናገሩት ነው እንጅ እኔ ከየትም አላመጣሁትም፣ ለማረጋገጥ ከፈለጋችሁ የጠከስኳቸውን የሐዲሳቱንና የቁርአኑን ክፍሎች ማየት ትችላላሁ፡፡ የውመል ቂያማ ላይ እንኳን ለሙስሊም ወንዶች አላህ ያዘጋጀላቸው ሴቶች ባይገርማችሁ ሰይጣን ያልደፈራቸውን ሴቶችን ነው ቆይ ቁርአኑን ላስነብባችሁ፡-

**ሱረቱል አል-ረህማን 55 ፡ 56**

በውስጣቸው ከበፊታቸው (ከባሎቻቸው በፊት) ሰውም ጃንም ያልገሰሳቸው ዓይኖቻቸውን (በባሎቻቸው ላይ) አሳጣሪዎች (ሴቶች) አልሉ

فِيهِنَّ قَاصِرَاتُ الطَّرْفِ لَمْ يَطْمِثْهُنَّ إِنسٌ قَبْلَهُمْ وَلَا جَانٌّ

*እዚህ ባሉት በስንቶቹ ሴት ሙስሊም ወገኖቻችን በጅን የመደፈር እጣ ደርሶባቸው፣ ለወንዶቹ ሙስሊሞች በጀነት ሌሎች ነጫጭ ሴቶች ተዘጋጀላቸው? በአላህ ፍትሃዊነት ላይ ብዙ ጥያቄ ያስነሳል፤ ቢሆንም ለጊዜው እርሱ ይቆይና ይህ አንቀጽ ከላይ የተባለውን ሃሳብ ደጋፊ መሆኑን ሳታስተውሉ የቀራችሁ አይመስለኝም፡፡ ታዲያ አላህ ስለ አጋንንት እስረኝነት የሚያወራ፣ የአጋንንት እስረኛ ነኝ እያለ እናንተም እስረኞች ናችሁ የሚል፣ ከሕይዎት አጋርዎት ከሚስትዎት ጋር የሚደርጉትን መልካም ነገር እንዲህ የሚያጎድፍና የአላህን ቃል የሚጻረር ነቢይ አላህ የሚልክ ይመስላችኋል? እናንት ሙስሊም ወገኖቼ አላህ ሰይጣን ለእናንተ ግልጽ ጠላት ነው፤ ጠላት አድርጋችሁ ያዙት ያለውን ነቢዩ ወዳጅ አድርገው መያዛቸው ምን የሚሉት ይሆን?*

16. *ነቢዩ ሙሐመድ ከጅኖች ጋር ያወሩት የነበረውን ሁሉ ለሱሃባዎቻቸው በየጊዜው ያስተላልፉ እንደ ነበር ተመልክተናል፡፡ ሁለት ምሳሌ ልስጥ፡- የጅኖች ምግብ ስለሆነው ነገር አላህ የነገራቸው ሳይሆን ጅኑ እራሱ የነገራቸው ነበር ፤ ሁለተኛው ለሰይጣን ማባረሪያነት አያተል ኩርሲን ስለ መቅራት አላህ ለነቢዩ ምንም አይነት አያት አላወረደላቸውም የሰሙት ምግብ ሊሰርቅ የመጣ ጅንን አቡ ሁሬይራ ሲይዙት ለአቡ ሁሬይራ ጅኑ ነግሮት ለነቢዩ ያስተላለፈውና ነቢዩ ከዛ ያዘዙት ነው፡፡ ይህንን ሳሂህ ከሆነው ሐዲስ* **ከአል-ቡኻሪ** *እንዲሁም* **የሱረቱል አል-በቀራህ 2 ፡ 255 ተፍሲርን ተፍሲር ኢብን ካሲር** *ላይ መመልከት ትችላላችሁ፡፡ እንግዲህ ነቢዩ ሙሐመድና ሰይጣን እንዲህ እየሆኑ እንዲህም እያደረጉ ቁርአኑ የወረደ ከሆነ ቁርአን ንጹህ የአላህ ቃል ነው ብሎ ለማለት ይቻላል?*

➢ *ከሌሎቹ ነቢያት ጋር በንጽጽር ሲታዩ አሁንም ጥያቄዎች ይዥጎደጎዳሉ፤ ንጽጽሩን በዚህ አለም ላይ ከነበሩትና ከሚኖሩት ሰዎች ይልቅ እርሳቸው እንደሚቀርቡት ካወሩለት ከጌታ ኢየሱስ ጋር እንመልከተው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በአገልግሎት ዘመኑ እንደ አላህ መልእክተኛ ሲመላለስ በአገልግሎቱ ይታይ የነበረውና በነቢዩ ሙሃመድ የታየው እጅግ የተለያየ ነበር፡፡ በተጨማሪ ሁለቱም በሰይጣን ላይ የነበራቸው አቋም ፍጹም የተለያየ*

ነበር፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ በሃዲሳቸው እንደተናገሩት ቁርአኑም ላይ እንደሰፈረው ሁሉም ነቢያት በአንድ ተውሂድ ከተላኩ ነቢዩ ሙሐመድም ከእነዚህ ነቢያት ጋር የተመሳሰለ አገልግሎት ሊኖራቸው ይገባ ነበር፡፡ ሆኖም ይህ ሲሆን ባለመታየቱ የአላህ መልዕክተኛ ነኝ ማለታቸው ጥያቄ አስነስቷል አንድ የቁርአን አንቀጽ ላስነብባችሁና ጥያቄዬን እቀጥላለሁ፡፡

**ሱረቱል አል-አንአም 6 ፡ 90**

እነዚያ (ነቢያት) እነዚያ አላህ የመራቸው ናቸው፡፡ በመንገዳቸውም ተከተል በርሱ በቁርአን ላይ ምንም ዋጋ አልጠይቃችሁም እርሱ ለዓለማት ግሳጼ እንጅ ሌላ አይደለም በላቸው፡፡

أُولَٰئِكَ الَّذِينَ هَدَى اللَّهُ ۖ فَبِهُدَاهُمُ اقْتَدِهْ ۗ قُل لَّا أَسْأَلُكُمْ عَلَيْهِ أَجْرًا ۖ إِنْ هُوَ إِلَّا ذِكْرَىٰ لِلْعَالَمِينَ

| **ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ** | **ነቢዩ ሙሃመድ** |
|---|---|
| ※ ልጅነቱ ከሰይጣን ንክኪ ነጻ ነበር ይህንን ነቢዩ እራሳቸው መስክረዋል<br><br>**ሱረቱል አሊ-ኢምራን 3 ፡ 36፣ ቡኻሪ 60 ፡ 71 ቅጽ 6** | ※ ገና እድሜያቸው ከሁለት አመት በታች እያሉም ሰይጣን ነበረባቸው፡፡<br><br>**ሳሂህ ሙስሊም 1 ፡ 311** |
| ※ በአገልግሎቱ ዘመን ብዙዎች ከሰይጣን እስራት ነጻ ይወጡ በሽተኞች ይፈወሱ ነበር፡፡<br><br>**ማቴ 4 ፡ 24**<br>ከዚህም የተነሳ ዝናው በመላው ሶሪያ ተሰማ ህዝቡም በተለያዩ በሽታዎች የታመሙትን በክፉ ደዌ የሚሰቃዩትን አጋንንት ያደሩባቸውን የሚጥል በሽታ ያለባቸውን ሽባዎችን ሁሉ ወደ እርሱ አመጡ ፈወሳቸውም ፡፡ | ※ በአገልግሎት ዘመናቸውም ሰይጣን ነበረባቸው፡፡ ስለነበረባቸው ነው ሰይጣን አለባችሁ እኔም አለብኝ እያሉ የተናገሩት፡፡ ለአንድ አመት ሙሉ ከሚስታቸው ጋር ሳይሆን ከማይታይ አካል ጋር ወሲብ ይፈጽሙ የነበረው መቼም ሳይሆን በአገልግሎታቸው ዘመን ነው፡፡ ነቢይነታቸው ከዚህ የድግምት ጥቃት አላዳናቸውም ነበር |
| ※ አጋንንት ባደሩበት ሰው ላይ ሆነው እርሱን ሲያዩት ይጨነቁ ይጮሁና ልታጠፋን መጣህን እያሉ ይርበተበቱ፣ | ※ ነቢዩ ደግሞ ወደ ሰይጣኖቹ መንደር ተጋብዘው ይሄዱ አብረዋቸውም ያድሩ ነበር፡፡ ስሞታቸውንም ሰምተው ትዕዛዝ |

| | |
|---|---|
| ሲያዛቸውም ከሰዎቹ ውስጥ ይወጡ ነበር፡፡<br><br>**ማቴ** 8 ፡ 29<br>እነርሱም የእግዚአብሄር ልጅ ሆይ ከእኛ ምን ጉዳይ አለህ? ጊዜው ሳይደርስ ልታሰቃየን መጣህን? እያሉ ጮሁ፡፡ | ያወጡ ነበር፡፡ ወንድማማችነት በመካከላቸው ተፈጥሯል፣ የእርሳቸው ቁራኛ ሰይጣን ይህንን አድርግ ያንን ተው ይላቸው ነበር፡፡<br><br>**ሳሂህ ሙስሊም** 39 ፡ 6757 |
| ※ የመጣበት ዋና አላማ የዲያብሎስን ስራ ለማፈራረስ ነበር፡፡<br><br>1 **ዮሐ** 3 ፡ 8<br>ዲያብሎስ ከመጀመሪያ አንስቶ ኃጢአትን የሚያደርግ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ የተገለጠው የዲያብሎስን ስራ ያፈርስ ዘንድ ነው፡፡ | ※ አላህ እንዴት አሳቡን በእርሱ ላይ እንዴት እንደቀየረ ባይታወቅም ነቢዩ ሙሃመድን ለሰይጣንም መልእክተኛ አድርጎ ላካቸው፡፡ በረገመው ሰአት ምን እንደተነጋገሩ መዘንጋት የለብንም፡፡<br><br>**ሱረቱል አል-ሂጅር** 15 ፡ 35-39<br>**ሱረቱል ዩሱፍ** 12 ፡ 104 |
| ※ በእርሱ አምነው ሊከተሉት ወስነው ለሚመጡት ነጻነትና እረፍት የሚሰጥ ጌታ ነው ፡፡<br><br>**ማቴ** 11 ፡ 28-29<br>እናንት ሸክም የከበዳችሁና የደከማችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም ዕረፍት እሰጣችኋለሁ፡፡ ቀንበሬን ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ እኔ በልቤ የዋህና ትሁት ነኝና ለነፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ<br><br>**ገላ** 5 ፡ 1<br>ክርስቶስ ነጻ ያወጣን በነጻነት እንድንኖር ነው | ※ ሰይጣን እንዳለባቸው፣ ከሰይጣን ተጽዕኖ ነጻ መሆን ለእነርሱ ከባድ መሆኑን ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ይነግሯቸዋል፡፡<br><br>How to protect yourself from jinn & shaytan page 34<br>**ሳሂህ ሙስሊም** 39 ፡ 6757 |
| ※ ለተከተዮቹ በሰይጣንና በስራው እንዲሁም በሰራዊቱ ላይ ሙሉ ስልጣን ሰጣቸው፡፡<br><br>**ማቴ** 10 ፡ 8<br>በሽተኞችን ፈውሱ ሙታንን አስነሱ ለምጻሞችን አንጹ አጋንንትን አስወጡ በነጻ የተቀበላችሁት በነጻ ስጡ<br>**ሉቃ** 10 ፡ 18-20<br>እርሱም እንዲህ አላቸው፡- ሰይጣን እንደ | ※ **ቁራኛ** የተደረገባቸውን ሰይጣንን በበላይነት መርገጥ ይቅርና ወደ ክፉ እንዳይወሰውሳቸው ማስለም እጅግ ከባድ መሆኑን፣ ገነት መግባትም ለአንድ ሙስሊም ጭንቅ መሆኑን፣ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ከቁራኛቸው እንደ ማይላቀቁ፣ ይህ ሁሉ በአላህ ውሳኔ የተደነገገባቸው መሆኑን ሰብከዋቸዋል፡፡ |

| | |
|---|---|
| መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ፡፡ እንግዲህ እባቡንና ጊንጡን እንድትረግጡ በጠላትም ሃይል ሁሉ ላይ ስልጣን ሰጥቻችኋለሁ የሚጎዳችሁም አንዳች ነገር አይኖርም ፡፡ ይሁን እንጅ መናፍስት ስለተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ <u>ስማችሁ ግን በሰማይ ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ ፡፡</u> | |

- የሁለቱን የአላህ መልዕክተኞች አገልግሎታቸው ምን ይመስል እንደነበር ጥቂቱን አይተናል፡፡ ሰማይ ከምድር እንደሚርቅ የማይገናኝ አገልግሎት ነበራቸው፡፡ ይህም ነቢዩ ሙሐመድ ከራሳቸው ቁርአን ጋር እንዲጋጩና ጥያቄ እንዲነሳ ያደርጋል፡-

17. ነቢዩ ሙሃመድ ቁርአኑ ላይ እንደሰፈረው እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ የአላህ መልዕክተኛ ከሆኑ፣ ደግሞም በእምነት መግለጫቸው እንዳወጁት በኢየሱስ ክርስቶስ በወረደው በኢንጅሉ የሚያምኑ ሰው ከነበሩ፣ በሰይጣን ላይ ያላቸው አቋም ለምን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተለየ ሆነ?
18. አላህ ሰይጣንን በረገመበትና ለልመናው ምላሽ በሰጠበት ሰአት ባሮቹን እንዳይነካ ለሰይጣን የሰጠው ማስጠንቀቂያ ከነቢዩ ሙሐመድ ይልቅ በኢየሱስ ክርስቶስና በተከታዮቹ ሕይወትና አገልግሎት እስካሁን ድረስ ተፈጻሚነት እያገኘ ይገኛል፡፡ አሁንም የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ተከታዮች ሰይጣንን በጌታቸው ስም ከሰዎች እያስወጡ በነጻነት እየኖሩ ይገኛሉ፡፡ ይህንን ወደ እነርሱ በመሄድ ማረጋገጥ ትችላላችሁ፡፡ እንዳልኩት ይህ ግን ምንም ነቢዩ ሙሐመድ በቁርአኑ ቢናገሩትም እርሳቸውና ተከታዮቻቸው እስካሁን ድረስ ባለ ቁራኛ ሰይጣን ናቸው፡፡ ይህ እየሆነ ያለው ነቢዩና ተከታዮቻቸው የማን ባሪያዎች ቢሆኑ ነው?
19. ነቢዩ ሙሐመድ ከአላህ ተቀበልኩ ብለው ያመጡት ቃል በራሳቸውና በተከታዮቻቸው ሕይወት ውስጥ ተግባራዊ ሆኖ የማይታይና የሰው ልጆች ሁሉ ጠላት ከሆነው ከሰይጣን እስራት ነጻ የማያወጣ ከሆነ ቁርአን ከአላህ የተላከ፣ መልአኩ ገብርኤልም ያመጣው የአላህ ቃል ነው ብሎ ማመን ይቻላል ?
20. አላህ **በሱረቱል አል-አንአም** 6 ፡ 90 ላይ ነቢዩ ሙሐመድ የቀደሙትን ነቢያት ፈለግ እንዲከተሉ ቁርጥ ያለ ትዕዛዝ ደርሷቸዋል፡፡ ሆኖም የታየው ተቃራኒው እንጅ የዚህ ትዕዛዝ ፍጻሜ አይደለም፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ከሆኑና ቁርአን የአላህ ቃል ከሆነ ሁለቱ ለምን በተግባር ተለያዩ?

21. ለእርሰዎ የአላህ መልዕክተኛ ብለው የሚቀበሉት፣ እራሱንና ተከታዮቹን ከሰይጣንና ከስርአቱ ነጻ የሚያወጣ ወይንስ እራሱና ተከታዮቹ ከሰይጣን ጋር ዘመዳሞቾች እንደሆኑና ከእርሱ ተጽእኖ ነጻ መሆን እንደማይቻል የሚናገር ነቢይ?

ውድ አንባቢ ለእኔ እራሱና ተከታዮቹን ከሰይጣንና ከተጽዕኖው ነጻ የሚያወጣ እርሱ የአላህ መልዕክተኛ እንደሆነ ሳምን ከሰይጣንና ከተጽዕኖው በታች እንደሆነ የሚናገር እርሱ የአጭበርባሪው የሰይጣን መልዕክተኛ እንደሆነ አምናለሁ ፡፡ ስለዚህ ነቢዩ ሙሐመድና ቁርአን ከአላህ ዘንድ ለሰው ልጆች ደህንነት የተላኩ መልዕክትና መልዕክተኛ ባለመሆናቸው ልቀበላቸው አልቻልኩም ፡፡ ለእነዚህ የነፍሴ ጥቄያዎች ትክክለኛ ምላሽ በማግኘቴ ደስ ብሎኛል ፡፡ ስለዚህ እውነት ህይወትና መንገድ የሆነውን የነጻነት ሁሉ ጌታ የሆነውን ጌታ ኢየሱስን በደስታ እየተከተልኩ እገኛለሁ፤ ለእናንተም የሚከተለውን መልዕክት ልኮላችኋል

**ዮሐ** 14 ፡ 6

ኢየሱስም እንዲህ አለው፡- መንገዱ እኔ ነኝ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፡፡

**ዮሐ** 11 ፡ 25-26
ትንሳኤና ሕይወት እኔ ነኝ በእኔ የሚያምን ቢሞት እንኳን በሕይወት ይኖራል፣ በእኔ የሚኖር የሚያምንብኝም ከቶ አይሞትም፡፡

**ዮሐ** 10 ፡ 27-28
በጎቼ ድምጼን ይሰማሉ እኔ አውቃቸዋለሁ እነርሱም ይከተሉኛል እኔም የዘለአለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ ከቶ አይጠፉም ከእጄም ሊነጥቃቸው የሚችል ማንም የለም፡፡

**ማቴ** 11 ፡ 28-30
እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ፡፡ ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና ለነፍሳችሁ እረፍት ታገኛላችሁ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና፡፡

ለዚህ ድንቅ ጥሪ ምላሽ መስጠትና ከሰይጣን ቁራኛነት ማረፍ፣ የዘለአለም ሕይወትንም ማግኘት ይፈልጋሉ? መንገዱ በጣም ቀላል ነው፡፡ አሁን ባሉበት ሆነው

የሚከተለውን ጸሎት ይጸልዩ፣ እርሱም ይሰማዎታል ምላሹንም ወዲያው ይቀበላሉ፤ አይጠራጠሩ፡-

- ❖ ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ ከእግዚአብሔር ተልከህ የመጣህ እውነተኛ የሕይዎት መልዕክተኛ እንደሆንክ አምናለሁ
- ❖ እኔም እራሴ ኃጢአተኛ ሰው እንደሆንኩ አምናለሁ
- ❖ ስለ ኃጢአቴ መስቀል ላይ መሞትህን መቀበርህን ከሞትም መነሳትህን አምናለሁ
- ❖ አሁን ኃጢአቴን ይቅር እንድትል የዘለአለምንም ሕይወት እንድትሰጠኝ እለምንሃለሁ
- ❖ አሁን ወደልቤ ግባ ሕይወቴንም እንድትመራ እፈቅድልሃለሁ
- ❖ የእግዚአብሄር ልጅ የመሆንን ስልጣን ስጠኝ
- ❖ ዓለምን ሰይጣንን እክዳለሁ ሕይወቴን ላንተ እሰጣለሁ፤ አሜን ፡፡

ውድ አንባቢ ይህንን ጸሎት ከልብ ሆነው በጸለዩበት ሰአት የእግዚአብሔር ልጅ የመሆንን ስልጣን ተቀብለዋል፡፡

**ዮሐ 1 ፡ 12**
ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚአብሄር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው

ቁራኛ የተባለው ሰይጣን ከእርሰዎ ሄዷል፣ አሁን እርሰዎ የበላይ ነዎት፣ የእግዚአብሄር ልጅ ሰለሆኑም የገነት ገቢዎች አባል ሆነዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የሕይወት ምግብ የሆነውን መጽሃፍ ቅዱስን ያንብቡ፣ እንዴት በመንፈሳዊ ሕይወትዎ ማደግ እንዳለብዎት ትምህርት ያገኙ ዘንድ እውነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ አማኞች ጋር በመሄድ ሕብረት ያድርጉ፡፡ እንኳን ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ በሰላም መጡ እንኳንም ደስ ያለዎት !!!!!!!!

**ዋቢ መጻህፍት ፡-**


*መጽሃፍ ቅዱስ*
*የአማርኛና የአረብኛ ቁርአን*
Asbab al-Nuzul, by Ali ibn Ahmad al-Wahidi
Tafsir al-Tustari, by Sahl b. Abd Allah al-Tustari
Tanwir al-Miqbas minTafsir Ibn Ababas.
Tafsir Ibn Kathir
Hadith Sahih al-Bukhari.
Hadith sahih Muslim
Hadith Sunan Abu DAwud
Hadith Mishkat-Ul-MAsabeeh
Sirat ibn Hisham, Abridged by Abdus-salam M.Harun
Protect yourself from the Jinn & shaytan, by Wahid Abd al-Salam Bali
The Jinn & Human Sikness, by Dr Abul-Mundhir Khalil
Hadith Sunan Jami at-Tirmidhi
Fat, Al-Qada wal Qadar, by Dr. Saeed Ismaeel


**ጥያቄና አስተያየት ካለውት የሚከተለውን አድራሻ ተጠቅመው ይላኩልን በፍጥነት ምላሽ እንሰጣለን**


**JEA.2001@yahoo.com**